الفقه الأكبر

ታላቁ ዕውቀት



إعداد: لفضيلة الشيخ د/صالح بن فوزان الفوزان

ትርጉም፣ አቡ ፣ ዓብዲል ዓዚዝ/ዩሱፍ አህመድ

بسم الله الرحمن الرحيم

መግቢያ

ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይገባው። አገልጋዩና መልእክተኛው በሆኑት ነብያችን ሙሐመድ ﷺ፣ በቤተሰቦቻቸው ፣ በባልደረቦቻቸው ፣ በእርሳቸው መመሪያ በተመሩ ፣ ሱናቸውን አጥብቀው በያዙ ፣ በእርሳቸው ጎዳና እስከፍርዱ ቀን በተጓዙት ላይ ሁሉ የአላህ ሶላት ፣ ሰላምታ እና በረካ ይስፈን ።

ከዚህ በኋላ...

ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል ፡-

"من يرد الله به خيرا يفقهه في الدين"

"አላህ መልካምን የሻለት ዲንን ያስገነዝበዋል።" *(ቡኻሪ፡71, ሙስሊም፡1037)*

የዚህ ሐዲስ መልእክት ፣ በዲኑ ግንዛቤን መስጠቱ አላህ ለባሪያው መልካምን እንደሻለት ፣ ግንዛቤን አለመስጠቱ ደግሞ መልካምን እንዳልሻለት ያመላክታል። በዚህም ዲንን መገንዘብ አንገብጋቢ ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

ዲንን መገንዘብ እንዳለብን አላህ በተከበረው መጽሐፉ ቅስቀሳ አድርጓል፡

﴿وَمَا كَانَ الْمُؤْمِنُونَ لِيَنفِرُواْ كَآفَّةً فَلَوْلاَ نَفَرَ مِن كُلِّ فِرْقَةٍ مِّنْهُمْ طَآئِفَةٌ لِّيَتَفَقَّهُواْ فِي الدِّينِ وَلِيُنذِرُواْ قَوْمَهُمْ إِذَا رَجَعُواْ إِلَيْهِمْ لَعَلَّهُمْ يَحْذَرُونَ﴾

"ምእመናንም (ከነብዩ ጋር ካልሆነ) በሙሉ ሊወጡ አይገባም። ከእነሱ ውስጥ ከየክፍሉ አንዲት ጭፍራ ለምን አትወጣም። (ሌሎቹ) ሃይማኖትን እንዲማሩና ወገኖቻቸው ወደነርሱ በተመለሱ ጊዜ እንዲጠነቀቁ ይገስጹዋቸው ዘንድ (ለምን አይቀሩም።" *(አት'ተውባህ፡122)*

ዲንን የማይገነዘቡ አካላትን ደግሞ አላህ አነውሯል።

﴿وَلَكِنَّ الْمُنَافِقِينَ لَا يَفْقَهُونَ﴾

“ግን መናፍቃን አያውቁም::” *(አል’ሙናፊቁን፡7)*

﴿فَمَا لِهَؤُلاء الْقَوْمِ لاَ يَكَادُونَ يَفْقَهُونَ حَدِيثًا﴾

“ስእነዚህም ሰዎች ንግግርን ሲፈጹ የማይቀርቡት ምን አሳቸው?!” *(አን’ኒሳእ፡78)*

የአላህን ዲን ያልተገነዘበ ፣ ለእርሱም ትኩረትን ያልሰጠ ፣ ትጉ ሆኖ እውቀትን ያልፈለገ ከመልካም ነገሮች የተነፈገ ማለት እርሱ ነው። ምክንያቱም ዲንን ሳይገነዘብ ፣ አላህ በሚወደው መልኩና እርሱ በደነገገው ሸሪዓ መሰረት አምልኮትን መፈጸም አይችልም።

ያለ ዲን ግንዛቤ አላህን የሚገዛና ተግባርን የሚፈጽም ፣ ተግባሩ በትክክለኛው መሰረት ላይ የተገነባ ሊሆን በፍጹም አይችልም። በአጠቃላይ ወይም አብዛኛው ተግባሩ ጥመት ሊሆን ይችላል።

በዚህ ቦታ የአላህን ዲን መገንዘብ አንገብጋቢና ታላቅ ነገር እንደሆነ ፤ እያንዳንዱ ሙስሊም አላህን እንዴት መግገዛት እንዳለበት ፣ ግዴታውን እንዴት መወጣት እንዳለበት ፤ ከሰዎች ጋር ፣ ከቤተሰቦቹ ፣ ከልጆቹ ፣ ከጎረቤቶቹ ፣ ከዘመዶቹ እና ከጓደኞቹ ጋር ባለው ግንኙነት ዲኑ ምን እንደሚል ፣ በአጠቃላይ ለሐቅ ባለቤቶች ሐቃቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲሰጥ ፣ የአላህን ዲን መገንዘብ እንዳለበት ማወቅ ችለናል።

የአላህን ሐቅ ፣ ከዚያም የባሮችን ሐቅ አስመልክቶ በዲኑ ግንዛቤ የሌለው ሰው በተፈላጊው መልኩ የሐቅ ባለቤቶችን ሐቃቸውን መስጠት አይችልም።

የፊቅህ ዓይነቶች

በዲን ውስጥ የሚገኘው ፊቅህ ሁለት አይነት ነው ፡

የመጀመሪያው፡ ዓቂዳን የምንገነዘብበት ፊቅህ

ዓቂዳን መገንዘብ የዲን መሰረት ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ ዓቂዳውን የሚያስተካክልበትን ፤ ሽርክም ይሁን ቢድዓ እምነቱን የሚሸረሸርበትን ወይም የሚቀንስበትን ማወቁ የግድ ነው። ዓቂዳን መገንዘብ ማለት የተውሒድን እምነት ፣ ለዚህ እምነት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማወቅ ማለት ነው። ይህ ብቻ አይደለም የእምነት ተቃራኒ ወይም እምነትን የሚሸረሸሩ እና የሚቀንሱ ነገሮችንም ማወቅ ማለት ነው።

ይህ የፊቅህ ዓይነት ዋና መሰረት ነው። ከአንዳንድ ዑለሞች ዘንድ (ፊቅሁል አክበር) በሚል ስያሜ ይጠራል። ይህም እያንዳንዱ ሰው ፈጣሪውን ፣ የፈጣሪውን ስሞችና ባህሪያቶቹን ማወቅ ማለት ነው። በአግባቡ አላህን እንዴት እንደሚገዛ ፣ የሰው ልጅ የተፈጠረበት ዓላማ ምን እንደሆነ? ጌታውን አስመልክቶ ከእርሱ የሚፋፈለጉ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሊርቃቸው የሚገቡ ምን ምን ነገሮችን ነው? የአላህን መብት አስመልክቶ የማይፈቀደው ምንድን ነው? የሚሉ ነገሮችን ማወቅ ማለት ነው።

ይህ የፊቅህ አይነት መሰረታዊ የፊቅህ ዓይነት ነው። እርሱም በአግባቡ ተፈጻሚ ሊያደርገው ዘንድ ሶስቱን የተውሂድ ክፍሎች - ተውሂደ ሩቡብያ ፣ ተውሒደ ኡሉሂያ እና ተውሂድ አስማእ ወስሲፋትን - የሚያውቅበት ፊቅህ ነው። ከእነዚህ የተውሂድ አይነቶች ጎን በጎን ፣ የተውሒድን ሐቆች ፣ ተውሒድን የሚያሟሉ ነገሮችን የሚያውቅበት ፣ ሊርቃቸው ዘንድ ተውሒድን የሚቃረኑ እና የሚጻረሩ የሽርክ ፣ የቢድዓ እና ሌሎች አፍራሽ ነገሮችን ማወቁ ግዴታ የሚሆንበት ነው። ይህ ካልሆነ ነገሮች በእርሱ ላይ ይምታቱበታል ፤ ሽርክ ችግር እንደሌለው አድርጎ ሊገምት ይችላል። በተለይም ተውሂድን በማያውቁ ፣ የሽርክ ምንነትን ጠንቅቀው በማይገነዘቡ አገሮች እና ትውልዶች ውስጥ ካደገ።

አላህ ከዚህ በፊት ስለነበሩት ህዝቦች ሁኔታ እንደነገረን ፣ በበርካታ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች መቃብር ላይ መገንባት ፣ በመቃብር ዙሪያ መጥወፍ ፣ ሙታኖችን መጠየቅ ፣ ሙታኖችን መጣራት ፣ ድረሱልኝ ማለት ፣ ከእነርሱ የተለያዩ ሐጃዎች እንዲፈጽሙላቸው መፈለግን የዲን አካል አድርገው የሚገምቱ አሉ።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጾች የሚከተለውን ተናግሯል ፡-

﴿وَيَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللهِ مَا لاَ يَضُرُّهُمْ وَلاَ يَنفَعُهُمْ وَيَقُولُونَ هَـؤُلاء شُفَعَاؤُنَا عِندَ اللهِ﴾

“ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይግገዛሉ:: “እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው” ይላሉ::” *(ዩኑስ፡ 18)*

﴿وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاء مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللهِ زُلْفَى﴾

“እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖትን) ረዳቶች አድርገው የያዙት “ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም” (ይላሉ):: *(አዝ’ዙመር፡3)*

አባቶቻቸውን ፣ አያቶቻቸውን ፣ የአገሮቻቸውን ሰዎች በዚህ ላይ ስላገኙ ብቻ ይህን ተግባር አላህ የሚወደው ተግባር እንዲሁም የዲኑ አካል አድርገው ይገምታሉ።

በዚህ ምክንያት አጋሪዎች የሚከተለውን ንግግር ተናግረዋል፡

﴿لَوْ شَاء اللهُ مَا أَشْرَكْنَا وَلاَ آبَاؤُنَا﴾

(እነዚያ ያጋሩት)“አላህ በሻ ኖሮ እኛም አባቶቻችንም ባላጋራን ነበር::” (ይላሉ) *(አል’አንዓም፡ 148)*

﴿لَوْ شَاء اللهُ مَا عَبَدْنَا مِن دُونِهِ مِن شَيْءٍ نَّحْنُ وَلا آبَاؤُنَا﴾

“አላህ በሻ ኖሮ ከእርሱ ሌላ እኛም አባቶቻችንም ምንንም ባልተገዛን ነበር::” *(አን’ነሕል፡ 35)*

በሚከተለው ቃሉ አላህ ምላሽ ሰጧቸዋል ፡-

﴿وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولاً أَنِ اعْبُدُواْ اللهَ وَاجْتَنِبُواْ الطَّاغُوتَ﴾

“በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ “አላህን ተገዙ : ጣዖትንም ፈቁ” በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል::” *(አን’ነሕል፡ 36)*

ይህን ተግባራቸውን አላህ ወዶት ቢሆን ኖሩ የእነርሱን ተግባር ለማውገዝ መልእክተኞችን ባልላከ ነበር። ይህን እምነት አጥብቀው የያዙበት ምክንያት ፣ አምልኮትን ፍጹም ለአላህ ለማድረግ ነብያቶች የመጡበት ወደሆነው ትክክለኛ መንገድ ባለመመለሳቸውና ማህይምነትን በመምረጣቸው ነው።

"በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ "አላህን ተገዙ ፡ ጣዖትንም ፈቁ" በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።" *(አን'ነሕል ፡ 36)*

ወልይ ወይም አማላጅ ወይም በማንኛውም ስም ቢጠራ ከአላህ ውጭ የሚመለክ ነገር ሁሉ ጣዖት ተብሎ ይጠራል። ከአላህ ውጭ መመለኩን ወዶ ተቀብሎ ከሆነ ይህ ጣዖት ነው። ሲመለክ የማይወድ ከሆነ ግን ጣኦት ተብሎ አይጠራም። ሰዎች ሲያመልኩት የማይወድ ፣ በሒዎት እያለ ከዚህ ተግባራቸው የሚከለክል ከሆነ ይህ እንደጣዖት አይቆጠረም። ነገር ግን አምልኮቱ በአላህ ማጋራት ነው። መመለካቸውን ሳይወዱ ፣ በአላህ ማጋራትን በሐይለኛው ሲያወግዙ ብሎም በዚህ ላይ ሲዋጉ የነበሩ ፣ ይሁን እንጅ ከሞቱ በኋላ መቃብራቸው ተገንብቶ ፣ የተለያዩ ቁርባን (መቃረቢያ) እየቀረበላቸው ከአላህ ውጭ የተመለኩ አሉ። እነዚህ እንደጣዖት አይታዩም። ኢሳ ﷺ ተመልኳል ፤ መላኢካዎች ተመልከዋል ፤ ደጋግ የአላህ ባሮች ተመልከዋል። ነገር ግን እነርሱን ያመለካቸው አካል ሙሽሪክ ነው።

አላህ የሚከተለውን ቁርኣናዊ አንቀጽ አውርዷል፡-

﴿إِنَّكُمْ وَمَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللَّهِ حَصَبُ جَهَنَّمَ أَنتُمْ لَهَا وَارِدُونَ﴾

"እናንተ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸውም (ጣዖታት) የገሀነም ማገዶዎች ናቸው። እናንተ ለእርሷ ወራጆች ናችሁ።" *(አል'አንቢያ፡98)*

ይህ የቁርኣን አንቀጽ ሲወርድ ሙሽሪኮች ተደሰቱ። "እኛ ኡዘይርን እናመልካለን ፣ መሲህን እናመልካለን ፣ መላኢካዎችን እናመልካለን ፤ እነዚህ ከእኛ ጋር እሳት ውስጥ ከሆኑ በእኛ ላይ ምንም ዓይነት ወቀሳ የለብንም" በማለት ተናገሩ።

በእነርሱ ላይ ምላሽ ለመስጠት የሚከተለውን ቁርኣን አላህ አወረደ።

﴿إِنَّ الَّذِينَ سَبَقَتْ لَهُم مِّنَّا الْحُسْنَى أُوْلَئِكَ عَنْهَا مُبْعَدُونَ﴾

"እነዚያ ከእኛ መልካሚ ቃል ለእነርሱ ያለፈችላቸው እነዚያ ከርሷ የተፈቁ ናቸው።" *(አል'አንቢያ፡ 101)*

ይህ ቁርኣን ፍላጎት ሳይኖራቸው ከአላህ ውጭ የተመለኩ ኢሳ ፣ ኡዘይር ፣ መላኢካዎች እና ሙእሚኖችን የሚመለከት ነው።

﴿إِنَّ الَّذِينَ سَبَقَتْ لَهُم مِّنَّا الْحُسْنَى أُوْلَئِكَ عَنْهَا مُبْعَدُونَ﴾﴿لَا يَسْمَعُونَ حَسِيسَهَا وَهُمْ فِي مَا اشْتَهَتْ أَنفُسُهُمْ خَالِدُونَ﴾﴿لَا يَحْزُنُهُمُ الْفَزَعُ الْأَكْبَرُ وَتَتَلَقَّاهُمُ الْمَلَائِكَةُ هَذَا يَوْمُكُمُ الَّذِي كُنتُمْ تُوعَدُونَ﴾

"እነዚያ ከእኛ መልካሚ ቃል ለእነርሱ ያለፈችላቸው እነዚያ ከርሷ የተፈቁ ናቸው። ድምጽዋን አይሰሙም። እነርሱም ነፍሶቻቸው በሚሹት ነገር ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። ታላቁ ድንጋጤ አያስተክዛቸውም።መላእክትም ይህ ያ ትቀጠሩ የነበራችሁት ቀናችሁ ነው። እያሉ ይቀበሏቸዋል።" *(አል'አንቢያ 101-103)*

መመለካቸውን ሳይወዱ ፣ ከሞቱ በኋላ የተመለኩ በትክክለኛ ዓቂዳ ላይ የሞቱ ሷሊሆች, እነዛ ሙሽሪኮች በፈጸሙባቸው ድርጊት ተጠያቂ አይሆኑም። ምክንያቱም እነርሱ በህይዎት እያሉ የሙሽሪኮችን ድርጊት አልወደዱም ፤ በአምልኮታቸው ሰዎችን አላዘዙም።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል ፡-

﴿مَا كَانَ لِبَشَرٍ أَن يُؤْتِيَهُ اللهُ الْكِتَابَ وَالْحُكْمَ وَالنُّبُوَّةَ ثُمَّ يَقُولَ لِلنَّاسِ كُونُواْ عِبَادًا لِّي مِن دُونِ اللهِ وَلَكِن كُونُواْ رَبَّانِيِّينَ بِمَا كُنتُمْ تُعَلِّمُونَ الْكِتَابَ وَبِمَا كُنتُمْ تَدْرُسُونَ﴾﴿وَلاَ يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُواْ الْمَلاَئِكَةَ وَالنَّبِيِّيْنَ أَرْبَابًا أَيَأْمُرُكُم بِالْكُفْرِ بَعْدَ إِذْ أَنتُم مُّسْلِمُونَ﴾

"ለማንም ሰው አላህ መጽሐፍንና ጥበብን ነብይነትንም ሊሰጠውና ከዚያም ለሰዎች "ከአላህ ሌላ ለእኔ ባሮች ሁኑ" ሊል አይገባውም። "ግን መጽሐፍን የምታስተምሩ በነበራችሁትና የምታጠኑም በነበራችሁት በእውቀታችሁ ሰፊዎች ሁኑ" (ይላቸዋል)። መላእክትንና ነብያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)። እናንተ ሙስሊሞች ከሆናችሁ በኋላ በክህደት ያዛችኋል?" *(አልዒምራን ፡79-80)*

﴿لَّقَدْ كَفَرَ الَّذِينَ قَالُواْ إِنَّ اللّهَ هُوَ الْمَسِيحُ ابْنُ مَرْيَمَ قُلْ فَمَن يَمْلِكُ مِنَ اللّهِ شَيْئًا إِنْ أَرَادَ أَن يُهْلِكَ الْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَأُمَّهُ وَمَن فِي الأَرْضِ جَمِيعًا وَلِلّهِ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا يَخْلُقُ مَا يَشَاء وَاللّهُ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ﴾

"በእርሱ ያዘዘከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ። በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።" *(አል'ማኢዳህ፡117)*

ከአላህ ውጭ መመለኩን የሚወድ ፣ ወደነፍሱ አምልኮ ሰዎችን የሚቀሰቅስ ጣዖት በመባል ይጠራል።

ከአላህ ውጭ ተፈጻሚ የሆኑ አምልኮቶችን እስካልተወ ድረስ የአላህ አምልኮ ትክክል አይሆንም።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡

﴿وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولاً أَنِ اعْبُدُواْ اللّهَ وَاجْتَنِبُواْ الطَّاغُوتَ﴾

"አላህን ተገዙ ፤ ጣዖትንም ፈቁ" በማለት መልእክተኛን በእርግጥ ልከናል።" *(አን'ነሕል፡36)*

﴿وَاعْبُدُواْ اللّهَ وَلاَ تُشْرِكُواْ بِهِ شَيْئًا﴾

"አላህንም ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ።" *(አን'ኒሳእ፡36)*

"አላህን ተገዙ።" በሚለው ቃሉ ብቻ አልቆመም። ይልቁንም "በእርሱም ምንንም አታጋሩ።" በማለት ጨምሮ ተናግሯል። ምክንያቱም ከሽርክ የጠራ ካልሆነ በቀር ፣ አምልኮ ምንም ጥቅም አይኖረውም።

﴿فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاء رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا﴾

"የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው ፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት እንድንም አያጋራ" በላችሁ።" *(አል'ከህፍ፡110)*

***"መልካም ስራን ይስራ"* ብሎ አላቆመም። ይልቁንም በእርሱ ማጋራትን ከለከለ። ምክንያቱም የሰው ልጅ መልካም ስራን ቢሰራም በአላህ ላይ በማጋራቱ ስራው ይበላሻል።**

በሰራው ስራ ምንም ሳይጠቀምበት ልክ እንደተበተነ አቧራ ይሆናል። ከሽርክ ካልጠራ መልካም ስራ ፋይዳ አይኖረውም። ይህ በጣም አደገኛ በመሆኑ ግንዛቤ ያስፈልገዋል። ሽርክ ምን እንደሆነ መታወቅ አለበት። ልንርቀው ፣ ልንከለክል ዘንድ ፣ አምልኮታችን ሰላም ይሆን ዘንድ ፣ ዲናችን ፍጹም ለአላህ ይሆን ዘንድ ሽርክ ምንድን ነው? የሽርክ አይነቶች ምን ምን ናቸው? የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል።

በዚህ ጉዳይ በርካታው ሰው ተዘናግቶ ይገኛል። የተውሂድን ትምህርት መማር ፣ የዓቂዳን ትምህርት መማር ፣ ወደአላህ አምልኮ መጣራት ሰዎችን እንደሚከፋፍል አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ። "እኛ የምንፈልገው ሰዎችን መሰብሰብ ነው" ይላሉ። እኛ ደግሞ "በተውሂድ ላይ ካልሆነ መሰባሰብ አይገኝም። ያለ ተውሂድ የሚደረግ ስብስብ ምንም መልካም የለውም ፣ ምንም ፋይዳ የለውም ፣ መጨረሻው ጠብና ጥላቻ ነው ፣ መጨረሻው መወገድ ነው" እንላቸዋለን።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

﴿وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُو مِن دُونِ اللَّهِ مَن لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُ إِلَى يَومِ الْقِيَامَةِ وَهُمْ عَن دُعَائِهِمْ غَافِلُونَ۝وَإِذَا حُشِرَ النَّاسُ كَانُوا لَهُمْ أَعْدَاء وَكَانُوا بِعِبَادَتِهِمْ كَافِرِينَ﴾

"እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስም ለእርሱ የማይመልስለትን (ጣዖት) ከአላህ ሌላ ከሚጣሩ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማንነው እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው። ሰዎችም በተሰበሰቡ ጊዜ (ጣኦቶቹ) ለእነርሱ ጠላቶች ይሆናሉ። (እነርሱን) መገዛታቸውንም ክዳዎች ይሆናሉ።" *(አል'አህቃፍ፡5-6)*

﴿الْأَخِلَّاء يَوْمَئِذٍ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ إِلَّا الْمُتَّقِينَ۝يَا عِبَادِ لَا خَوْفٌ عَلَيْكُمُ الْيَوْمَ وَلَا أَنتُمْ تَحْزَنُونَ﴾

"ወዳጆች በዚያ ቀን ከፊሎቹ ለከፊሉ ጠላት ነው። አላህን ፈሪዎች ብቻ ሲቀሩ። (ለነርሱ) "ባሮቼ ሆይ! ዛሬ ቀን በእናንተ ላይ ፍርሃት የለባችሁም እናንተም የምታዝኑ አይደላችሁም" (ይባላሉ) *(አዝ'ዙኽሩፍ፡67-68)*

በትክክለኛ ዓቂዳ ላይ ካለሆነ በቀር ፍሬያማ ስብስብ አይኖርም። በመሆኑም ትክክለኛ የሆነውን ዓቂዳ ማወቅ ግዴታችን ነው። ሁልጊዜ ወደርሱ ጥሪ የማድረግ ግዴታም አለብን። እርሱን ልንማር

፣ ስለርሱ ልንጠይቅ ፣ በትምህርት ቤቶቻችን ፣ በየኢንስቲቱዩቱ ፣ በየኮሌጆቹ ልናስተምረው ይገባል። ምክንያቱም እርሱ መሰረት ነው ፣ ትልቁ የዲን እውቀትም ነው።

ሁለተኛው አይነት፡ ተግባራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ፊቅህ

በሶላት ፣ በዘካ ፣ በጾም ፣ በሐጅ ፣ በሽያጭና ግዥ ፣ በጋብቻ ፣ በፍች ፣ በዒድዳ ፣ በትልቁና በትንሹ ንጽህና እና በመሳሰሉ የሸሪዓ ህግጋቶች ዙሪያ ማወቅ ለመጀመሪያው የዓቂዳ ፊቅህ ማሟያ እንዲሁም ለእርሱ ተከታይ ነው። : ትልቁ ፊቅህ ካልተረጋገጠ ይህ ፊቅህ ጠቀሜታ አይኖረውም።

አንድ ሰው ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ፣ በሶላት ፣ በዘካ ፣ በጾም እና በሐጅ ህግጋቶች ላይ ልክ እንደባህር የጠለቀ የፊቅህ እውቀት ቢኖረው ትልቁን ፊቅህ የማያውቅ ከሆነ ወይም በእርሱ ዙሪያ ቸልተኛ ከሆነ የሚሰጠው ፋይዳ አይኖረውም። ምክንያቱም ትልቁ የዓቂዳ ፊቅህ ወይም ተውሂድ ካልተረጋገጠ ሶላቱ ፣ ዘካው ፣ ጾሙ ፣ ሐጁ ፣ ዑምራው ትክክል አይሆንም። ማንኛውም ዒባዳ ትክክል አይሆንም።

ከዚህ በፊት እንዳወሳንላችሁ በርካታ ሰዎች በሁለተኛው ፊቅህ ላይ ትኩረት ሰጠው በመጀመሪያው ፊቅህ ዙሪያ ቸልተኝነት ቢያሳዩም ፣ ሁለተኛው ፊቅህ (ተግባራዊ ነገሮችን የምንገነዘብበት ፊቅህ) ለመጀመሪያው (ተውሂድን ለምንገነዘብበት) ፊቅህ ማሟያ እና ተከታይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል። ይህ ትልቅ ማህይምነት እና ትልቅ የሆነ ጉድለት ነው። የዚህ ሰው ምሳሌ ከአንገት በላይ የተቆረጠን አካል ህክምና እንደመስጠት ነው። ራሱ የተቆረጠ አካል በተለያየ መድሀኒት ብታክመው ፣ ጥንብ እና ደረቅ በመሆኑ ምንም የሚሰጠው ጥቅም የለውም።

በሁለቱም ዓይነት ፊቅህን የምናገኝባቸው መንገዶች

የፊቅህን አንገብጋቢነት ፣ የፊቅህን ክፍሎች ፣ በዲን ውስጥ ሁሉም ክፍሎች ያላቸውን ደረጃ ካወቅን በኋላ የዲን ግንዛቤ እውቀትን ለማግኘት የሚወስዱ መንገዶችን ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል።

አንደኛ ፡- መማር

በዲን ውስጥ ያለው ግንዛቤ የሚገኘው በትምህርት ቤት ክፍሎች ፣ በሀለቃዎች ፣ በስርዓተ ትምህርት በሚመሩ መድረሳዎች ከመምህር ፊት ቁጭ ብሎ በመማር ነው። ይህ ወደእውቀት ለመድረስ የመጀመሪያው እና መልካም የሆነው መዳረሻ ነው። ከዑለሞች እጅ ትምህርት መውሰድ ፣ በመስጅድም ይሁን በትምህርት ቤት ወይም በማንኛውም ቦታ በዚክር ሀለቃዎች ተቀምጦ ዲናዊ ትምህርትን መከታተል።

ገጣሚው የሚከተለውን ተናግሯል ፡-

من لم يذق ذل التعلم ساعة
تجرع كأس الجهل طول حياته

ለሰዓት ያልቀመሰ ፣ የመማር መተናነስ
ዘላለም ይጎነጫል ፣ የማህይምነትን ከእሰ (ዋንጫ)

የሰው ልጅ በእውቀቱ አይኩራ። “እኔ ደረጃ ያለኝ ሰው ነኝ ፤ መስጅድ ውስጥ ወይም መድረሳ ወይም የትምህርት ቤት ክፍሎች ውስጥ ከዓሊሞች ፊት ለፊት መቀመጥ ከእኔ ጋር የሚሄድ አይደለም ፤ ከዚህ ተግባር የጠራሁ ነኝ” አትበል። ይህ ስህተት የሆነ ተግባር ነው። የግድ መቀመጥ አለብህ። እውቀትን ለመፈለግ ሲባል ነፍስህን አስታግሳት። እውቀት ለማግኘት ስትል የሚደርስብህን ልፋት እና መከራ በትዕግስት ልትቀበል ይገባሃል። ለእውቀት ሲባል ጭንቀትን ፣ እንቅልፍ ማጣትን ፣ ከዓሊሙ ፊት ለፊት ለረጅም ሰዓታት መቀመጥን በትዕግስት ልትሸከም ይገባሃል። ካለበለዚያ ጀሂል ሆነህ ትኖራለህ። እድሜ ልክህን የማህይምነት ዋንጫ ስትጎነጭ ትኖራለህ።

እውቀትን ለመፈለግ ሞይል አካላት

ታማኙ መንፈስ ጅብሪል ﷺ ወደረሡል ﷺ ሶሃቦች በታደሙበት ድንገት መጣ። ዑመር ﷺ ታሪኩን እንደሚከተለው ይነግረናል ፡

“ከነብዩ ﷺ ዘንድ ተቀምጠን ባለንበት መካከል ልብሱ በጣም የነጻ ፣ ጸጉሩ በጣም የጠቆረ ፣ የተጓዥነት ምልክት የማይታይበት ፣ ከእኛ መካከል አንድም ሰው የማያውቀው ግለሰብ ገባ። ከነብዩም ዘንድ ተቀመጠ ፤ ጉልበቱን ወደጉልበታቸው አስጠጋ ፤ እጆቹን ከጭኖቹ ላይ አኖረ። “ሙሐመድ ሆይ ስለኢማን ንገረኝ” አላቸው። እርሳቸውም “ኢማን ፡ በአላህ ፣ በመላኢካዎች ፣ በመጽሐፎች ፣ በመልእክተኞች ፣ በመጨረሻው ቀን ፣ መልካምም ይሁን ክፉ በአላህ ውሳኔ ልታምን ነው።” በማለት ምላሽ ሰጡት። እርሱም “እውነትክን ነው” አላቸው። “ጥያቄ ጠይቆ ፣ እውነትክን ነው በማለቱ ተደነቅን” በማለት ዑመር ይናገራል። ከዚያም ፡ “ስለኢስላም ንገረኝ” አላቸው። “ኢስላም ላኢላሃ ኢልለሏህ ሙሐመድ ረሡሉሏህ ብለህ ልትመሰክር ፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቀህ ልትሰግድ ፣ ዘካ ልታወጣ ፣ የረመዷንን ጾም ልትጾም ፣ ወደርሱ መንገድን ከቻልክ ሐጅ ልታደርግ ነው” አላቸው። በሌላ ዘገባ “ቤቱን ልትጎበኝና ዑምራ ልታደርግ ነው።” አላቸው። “እውነትክን ነው ፣ ስለኢህሳን ደግሞ ንገረኝ” አላቸው። እርሳቸውም “ኢህሳን አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልትገዛው ነው። የማታየው እንኳ ቢሆን እርሱ ይመለከትሃልና” በማለት መለሱለት። “እውነትክን ነው” አላቸው። “ስለ (ቂያማ) ሰዓት ንገረኝ” አላቸው። “ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ አያውቅም” በማለት መለሱለት። ይህ ማለት በዚህ ጉዳይ አንተም እኔም እኩል ነን። ቂያማ መቸ እንደሚቆም ሰዓቱን ሁላችንም አናውቀውም ፤ ይህ ከአላህ በስተቀር የሚያውቀው የለም ማለታቸው ነው።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል ፡-

﴿إِنَّ اللَّهَ عِندَهُ عِلْمُ السَّاعَةِ﴾

“አላህ የሰዓቲቱ ሰዐቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው።” *(ሉቅማን 34)*

﴿يَسْأَلُكَ النَّاسُ عَنِ السَّاعَةِ قُلْ إِنَّمَا عِلْمُهَا عِندَ اللَّهِ وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّ السَّاعَةَ تَكُونُ قَرِيبًا﴾

“ሰዎች ከሰዓቲቱ ይጠይቁሃል። “እውቀትዋ ለኅህ ዘንድ ብቻ ነው፤” በላቸው። የሚያሳውቁህም ምንድን ነው! ሰዓቲቱ በቅርብ ጊዜ ልትሆን ይከጀላል።” *(አል’አህዛብ፡63)*

﴿يَسْأَلُونَكَ عَنِ السَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَاهَا﴾﴿فِيمَ أَنتَ مِن ذِكْرَاهَا﴾﴿إِلَى رَبِّكَ مُنتَهَاهَا﴾

“ከሰዓቲቱ መች ነው መሆኟዋ” ሲሉ ይጠይቁሃል። አንተ እርሷን ከማስታወስ በምን ውስጥ ነህ? (የእውቀት) መጨረሻዋ ወደ ጌታህ ብቻ ነው።” *(አን’ናዚዓት፡42-44)*

﴿يَسْأَلُونَكَ عَنِ السَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَاهَا قُلْ إِنَّمَا عِلْمُهَا عِندَ رَبِّي لاَ يُجَلِّيهَا لِوَقْتِهَا إِلاَّ هُوَ﴾

“ከሰዓቲቱ መቼ እንደምትረጋ (እንደምትመጣ) ይጠይቁሃል። “እውቀቷ ከጌታዬ ዘንድ ነው። በጊዜዋ እርሱ እንጂ ሌላ አይገልጣትም።” *(አል’አዕራፍ፡187)*

ነብዩ “ስለርሷ ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ አዋቂ አይደለም” በማለት ለጅብሪል መለሱለት። “ስለምልክቶቿ ንገረኝ” አላቸው። ቂያማ የሚቆምበት የሰዓቷ መጨረሻ ምልክት ይሆናል። እርሷ ይፋ ከሆነች የቂያማ ቀን መቆሙ ቅርብ መሆኑን ያመላክታል። እነርሱም ምልክቶች ብዙ ናቸው። ከእነርሱ መካከል ታላላቅ እና ከእነርሱ በታች የሆኑ ምልክቶች አሉ። “ሴት ባሪያ ጌታዋን - ማለትም አለቃዋን - ልትወልድ ነው። ጫማ የለሽ ፣ ራቁት የሆኑ ፣ ፍየል ጠባቂዎችን በግንባታ ሲፎካከሩ ልትመለከት ነው” በማለት ምላሽ ሰጡት። ከቂያማ ምልክቶች መካከል የገጠር ዓረቦች ጠንካራ ግንባታዎችን በመስራት መፎካከራቸው ነው። ምክንያቱም የገጠር ሰዎች ባህሪ መጓዝ ፣ የዝናብ ቦታዎችን መከታተል ነው። ቤት አይገነቡም ፣ በመንደሮችና በከተሞች አያርፉም። ነገር ግን መጨረሻ ዘመን ላይ በየከተማው በየመንደሩ መኖር ይጀምራሉ። ቤት ይገነባሉ ፣ በግንባታ ይፎካከራሉ። ይህ የቂያማ ምልክት ነው። ከዚያም ከነብዩ ጋር ፕሮግራሙን ሲጨርስ ግለሰቡ ወጣ ሄደ። አውሪታው የሚከተለውን ተናገረ ፡ “ረዘም ላለ ጊዜ ቆየን ፣ ከዚያም ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ተናገሩ፡- “ጠያቂው ማን እንደሆነ አውቃችኋል?” በማለት ሶሃቦችን ጠየቁ “አላህና የአላህ መልእክተኛ አዋቂ ናቸው” በማለት መለሱ። “ይህ ጅብሪል ነው። የዲናችሁን ጉዳይ ሊያስተምር ወደአናንተ መጦ ነው” *(ሙስሊም፡8)*

ጅብሪል የመጣው የሙሀመድ ኡመት ዲናቸውን እንዴት መማር እንዳለባቸው ፣ ከአስተማሪ ፊት ለፊት በስርዓትና በአክብሮት እንዴት መቀመጥ እንደሚቻል ለማስተማር ነው። ጅብሪል ሶሃቦችን ለማስተማር ወይም ኡመቶቻቸው እውቀትን በስርኣት እንዴት መውሰድ እንደሚችሉ ለማስገንዘብ ከነብዩ ﷺ ፊት ለፊት ልክ ተማሪ ከአስተማሪው ፊት ለፊት እንደሚቀመጠው በስርዓት እና በአክብሮት ነበር የተቀመጠው። ተማሪዎች ይጠይቃሉ ፣ አስተማሪው ለሁሉም ጥያቄ መልስ ይሰጣል። በዚህ ሐዲስ ውስጥ ከዑለማ ትምህርትን መውሰድ አንገብጋቢ እንደሆነ ፣ አንድ ሰው ትምህርት ሲቀስም ከዑለሞች ፊት ለፊት መቀመጥ እንደሚገባው ፣ ከዑለሞች ጋር ያለውን ስነስርዓት ፣ አጠያየቃቸው ምን መምሰል እንዳለበት ግንዛቤን ይሰጠናል።

ሙሳ ﷺ በምድር ላይ ከእርሱ ዘንድ የሌለ እውቀት ያለው አንድ ሰው አለ መባልን የሰማ ጊዜ የሚከተለውን ተናገረ፡

﴿قَالَ لَهُ مُوسَى هَلْ أَتَّبِعُكَ عَلَى أَن تُعَلِّمَنِ مِمَّا عُلِّمْتَ رُشْدًا ۝ قَالَ إِنَّكَ لَن تَسْتَطِيعَ مَعِيَ صَبْرًا﴾

“ከተማርከው ነገር ቀጥተኛን (እውቀት) ታስተምረኝ ዘንድ ልከተልህን” አለው። (ባሪያውም) አለ ፡ “አንተ ከእኔ ጋር መታገስን በጭራሽ አትችልም።” *(ኦል’ ከህፍ፡66-67)*

የአላህ አነጋጋሪ የሆነው ሙሳ ﷺ እውቀትን ለመፈለግ በችግሩ ላይ ታግሶ ረጅም ርቀትን ተጓዘ። ከዚህ ታሪክ የምንገነዘበው ችግር ፣ ልፋት እና ሰፈር ሳይኖር ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከህብረተሰብ መገለል ሳይኖር ኢልም እንዲሁ ሊገኝ እንደማይችል ነው።

ሁለተኛው፡ ከእውቀት መዳረሻዎች መካከል ቁርኣንን አስተንትኖ ማንበብ ነው

ቁርኣንን በምትቀራ ጊዜ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ፣ ቃላቶች የሚጠቁሙት መልእክት ምን እንደሆነ በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል። ቁርኣንን እንዲሁም የረሡልን ﷺ ንግግር ለመገንዘብ ታማኝና ትክክለኛ ወደሆኑ የተፍሲር ኪታቦች መዞር እንጂ ከእራስ መፍጠር ተገቢ አይደለም። የረሡልን ﷺሐዲስ ባነበብክ ጊዜ ቃሉን ብቻ ቀርተህ እንዲሁ ዝም ብለህ ማለፍ አይገባም። የግድ ትርጉሙን ምን እንደሆነ ፣ የረሡል ﷺ ፍላጎት ምን እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሐዲስን ለመገንዘብ ወደማብራሪያዎች መመለስ እንጅ ከራስ መፍጠር ተገቢ አይደለም። የፊቅህ ፣ የዓቂዳ ፣ የቋንቋ ኪታቦች በብዛት ማንበብ (መማር) ያስፈልጋል።

ሶስተኛው፡ ኪታቦችን በብዛት ካነበብን በኋላ ወደ እውቀት ለመድረስ የእውቀት ባለቤቶችን መጠየቅ ያስፈልጋል

የማታውቀውን ነገር የእውቀት ባለሌቶችን አደራ ጠይቅ። አላህ የሚከተለውን ተናግሯል ፡

﴿فَاسْأَلُواْ أَهْلَ الذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لاَ تَعْلَمُونَ﴾

"የማታውቁም ብትሆኑ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ::" *(አል'አንቢያ፡7)*

አይነ አፋርነት ጥያቄ ከመጠየቅ አይከልክልህ። የእውቀት ባለቤቶችን ከመጠየቅ የሚከለክል አይነ አፋርነት የተመሰገነ አይደለም። ይህ ፍርሃትና ድክመት እንጅ ሌላ አይደለም። የእውቀት ባለቤቶችን ከመጠየቅ ኩራት አይከልክልህ። አንዳንድ ሰዎች ዑለማዎችን ከጠየቅን ክብራችን ይጎድላል ብለው የሚያስቡ አሉ። ትክክለኛው ግን የእውቀት ባለቤቶችን መጠየቅ ውርደት ሳይሆን ሙሉነት ፣ ወንድነት ነው። ጥያቄው የድርቅና ወይም እራስን ከፍ ለማድረግ የታሰበበት ካልሆነ በቀር ዑለማን መጠየቅ ቅስቀሳ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። ዑለሞችን ሲጠይቅ እራሱን ከፍ አድርጎ ለማሳየት ዑለሞችን ደግሞ ዝቅ ለማድረግ ታስቦበት ከሆነ ክልክል ነው።

ዓብዱላህ ብን ዓባስ ﷺ "እውቀት እንዴት አገኘህ" ተብሎ ሲጠየቅ ፡

"ጠያቂ በሆነ አንደበት ፣ በሚገነዘብ ልቦና" የሚል ምላሽ ሰጧል። *(ኢማሙ አህመድ ፊ'ፈዷኢሊ ሶሃባ፡ 2/970)*

"ጠያቂ በሆነ አንደበት" ማለት የእውቀት ባለቤቶችን በብዛት መጠየቅ ማለት ነው። "የሚገነዘብ ልቦና" ማለት ደግሞ የተነገረውን የሚገነዘብ ልቦና ማለት ነው። በዚህም ቀስ በቀስ እውቀት ይገኛል።

ሙጃሂድ ብን ጀብር አታብኢይ አልጀሊል ﷺ የሚከተለውን ተናግሯል ፡

"እውቀትን አይነ አፋርና ኩራተኛ አያገኝውም" *(ቡኻሪ በሶሂህ ኪታባቸው ባቡ አልሓያኡ ፊል ዒልም ላይ በተሰላ ቅ ዘግቦታል)*

አራተኛው፡ እውቀትን ለመፈለግ በየሳምንቱ የሚደረጉ ኹጥባዎችን ፣ በየመስጅዱ የሚደረጉ ዳዕዋዎችንና ሙሐዶራዎችን ማዳመጥ

በጁሙዓ ኹጥባ ላይ ከተገኘህ ፣ የተነገሩ መልእክቶችን አዳምጠህ ያልገባህን ከጠየክ ፣ በየሳምንቱ የተለያዩ መልእክቶች ሲጠራቀሙና ሲደራጁ ለአንተ ትልቅ እውቀት ይሆናሉ። የጁሙዓ ኹጥባ የተደነገገው ሰዎችን ለማስተማር ፣ ለማስገንዘብ ፣ ለማስታወስ ሲባል ነው። በአሁኑ ሰኣት ሰዎች የጁሙዓ ኹጥባን ከማዳመጥ ተዘናግተዋል። በርካታው ሰው ኢቃም ሲደረግ ወይም የሶላቱ አንድ ረከዓ አልፎ ወይም ሲሰላመት ነው የሚደርሱት። ይህ ተፈላጊ የሆነውን ታላቅ ነገር መከልከል ነው።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا نُودِي لِلصَّلَاةِ مِن يَوْمِ الْجُمُعَةِ فَاسْعَوْا إِلَى ذِكْرِ اللَّهِ وَذَرُوا الْبَيْعَ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ﴾

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ በአርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ሂዱ። መሸጥንም ተው። ይህ የምታውቁ ብትሆኑ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው።” *(ጁሙዓ ፡ 9)*

“ዚክሩላህ” በማለት የተፈለገው ኹጥባው ወይም ሶላቱ ነው። መሰረታዊው ጉዳይ ግን ኹጥባው እንደሆነ በምዕራፉ መጨረሻ ላይ የሚገኘው የሚከተለው ሐሳብ ይጠቁማል፡-

﴿وَإِذَا رَأَوْا تِجَارَةً أَوْ لَهْوًا انفَضُّوا إِلَيْهَا وَتَرَكُوكَ قَائِمًا﴾

“ንግድን ወይም ዛዛታን ባዩ ጊዜም ቆመህ የተውህ ሲሆኑ ወደእርሷ ይበተናሉ።” *(ጁሙዓ ፡ 11)*

ጁሙዓ መገኘት በርካታ መልካም ነገሮችን ያስገኛል። አለመገኘት ደግሞ መልካም ነገሮችን ያሳጣል። ለዚህ ነው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ኹጥባው እስከሚያልቅ ድረስ ማንኛውም ሰው ዝም እንዲል ወይም እንዳይናገር እና እንዳይንቀሳቀስ የታዘዘው።

አምስተኛው፡ ጠቃሚ የሆኑ የሚልምና የዳዕዋ ስርጭቶችን ማዳመጥ

አንድ ሰው የሚሰራጩ የዳዕዋ ፕሮግራሞችን ልብ ብሎ ከተከታተለ እና ጉጉቱ ካለው ጥልቅ የሆኑ እውቀቶችን ፣ ፈታዋዎችን ያገኛል። በሚሰራጩ የሬዲዮ ፕሮግራሞች የዑለማዎች የተለያዩ

የዒልም ዝግጅቶች ይኖራሉ። ዑለሞች ለሰዎች ስለዲን እውቀት ያብራራሉ። ከቤትህ ወይም ከመኪናህ ውስጥ በቀላሉ ከፍተህ የቁርኣን ስርጨት እና የዳዕዋ ፕሮግራሞችን ታዳምጣለህ። ይህም ለአንተ ብዙ እውቀትን ያስገኝልሃል። ከተኛህበት ትነቃለህ ፣ የዘነጋሃውን ታስታውሳለህ ፣ የማታውቀውን ታውቃለህ።

ነገር ግን ከዚህ ፕሮግራም የምትርቅና የምትዘናጋ ፣ ምንም ቦታ የማትሰጠው ከሆነ ፣ እንዲሁም ከዓሊሞች ዘንድ ቀርበህ ኪታብ ካልቀራህ ፣ ሙሀደራ ካላዳመጥክ ወይም የጁሙዓ ኹጥባ ፣ በሬዲዮ የሚተላለፉ የዒልምና ፈትዋ ፕሮግራሞችን የማትከታተል ከሆነ ዒልም ከየት ይገኝልሃል! እድሜ ልክህን በጅህልና ላይ ትኖራለህ። ምናልባት አላህን በጅህልና እና በጥመት ልትገዛው ትችላለህ። ይህ ከሆነ ከዒባዳህ ምንም ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም።

አላህ እናንተንም እኔንም የዲን ግንዛቤና መልካም ስራን እንዲለግሰን ፤ ሀቅን በሀቅነቱ አሳይቶ መከተሉንም እንዲለግሰን ፣ ባጢልን በባጢልነቱ አሳይቶ መራቅንም እንዲለግሰን አላህን እማጸናለሁ።

والحمد لله رب العالمين وصلى الله وسلم وبارك على عبده ورسوله نبينا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين



ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐዶራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ሊንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alaterigilhaq